# ቅን ልቦና ከቤተሰብ ሕጉ አንፃር፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 25165• ፍርድ ላይ የቀረበ አስተያየት

ቤዛ ደሳለኝ ♣

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ አቶ አህመድ አብዱልሀሚድ (በሰበር ክርክሩ ተጠሪ) ክርክሩ በተጀመረበት በፌ/ከ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩ ሲሆን በአቶ እርቁ ጎዳ (በሰበር ክርክሩ አመልካች) እና አሁን በሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ላይ ጥቅምት 30 ቀን 1996 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ሁለተኛ ተከሳሽ (ወ/ሮ ወይንሸት ካሳሁን) ጋር ሚያዚያ 7 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ የባህል ጋብቻ መመሥረታቸውን፣ ይህንኑ ጋብቻም ሰኔ 3 ቀን 1992 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ማስመዘገባቸውን ገልፀው አንደኛ ተከሳሽ (አቶ ውሂብ ማዘንጊያ) ከሁለተኛ ተከሳሽ በተሰጠው የውክልና ሥልጣን ስሙ በሁለተኛ ተከሳሽ የሚገኘውን ሆኖም የጋራ ንብረታችን የሆነውን ቤት ያለ እኔ (ተጠሪ) እውቅና ለሦስተኛ ተከሳሽ (አመልካች) መጋቢት 5 ቀን 1994 ዓ.ም በተፈረመ ውል በብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) የተሸጠ ቢሆንም የገንዘቡ መጠን ዝቅ በማድረግ የተሸጠው በብር 23,000 (ሃያ ሦስት ሺህ) ነው የሚል መጋቢት 12 ቀን 1994 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው ውል ተፈራርመዋል። ይህም የሚያሳየው የቤት ሽያጭ ውሉ የተደረገው ከቅን ልቦና ውጭ መሆኑን ነው:: ስለሆነም ይኸው ውል ፈርሶ የባለቤትነት ስሙ በሁለተኛ ተከሳሽ ስም እንዲመዘገብ ይደረግልኝ ሲሉ ጠይቀዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩን በውክልና መሠረት በፈፀምኩት ውል ልከሰስ አይገባም በሚል ያቀረቡትን መቃወሚያ በመቀበል ከክሱ ያሰናበታቸው ሲሆን አመልካች ውሉን በፈፀምኩበት ወቅት ሁለተኛዋ ተከሳሽ ትዳር እንዳላት እንደማያውቁ ክደው የተከራከሩት በተጠሪ ያልተስተባበለ በመሆኑ አመልካች በቅን ልቦና በተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል መሠረት በሕጉ አግባብ የባለቤትነት መብት ያገኙትን ንብረት ሊያጡ አይገባም ሲል የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል። ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበዋል።

ይግባኙ የቀረበለት የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1266 እና አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 68 (1) (ሀ) ን በመጥቀስ በማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረት ላይ ለመዋዋል የሁለት ተጋቢዎች ስምምነት ያስፈልጋል፣ ማስረጃውን የሰጠው ቀበሌም ሁለተኛዋ ተከሳሽን በነዋሪነት ያልመዘገበ ከመሆኑም በላይ ስለጋብቻው መኖር አለመኖር ለማስረዳት ብቃት የለውም፣ ከዚህ እና ሁለት የተለያዩ የሽያጭ ዋጋ ያላቸው ውሎች በተዋዋዮቹ ከመደረጋቸው አንፃር የውሉ አደራረግ ለህሊና ብቻ ሳይሆን ለሕግም ተቃራኒ ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 69 (1) መሠረት ሊፈርስ ይገባዋል ሲል የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሯል።

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ችሎቱ የሰጠው ውሳኔ አመልካች ቤቱን ሲገዙ ስለ ሁለተኛ ተከሳሽ ጋብቻ ሁኔታ ከቀበሌ ማስረጃ መጠየቃቸው የቀበሌ ጽ/ቤት የነዋሪዎችን አሰፋፈርና የአኗኗር ሁኔታ በተመለከተ ከማንኛውም ተቋም በተሻለ መረጃዎችን ሰብስቦ የሚመዘግብ ከመሆኑ አንፃር መረጃው አግባብነት ያለው ነው። የሽያጭ ውሎቹን በተመለከተ መጋቢት 12 ቀን 1994 ዓ.ም የተደረገው በውልና ማስረጃ የፀደቀ ሲሆን መጋቢት 5 ቀን 1994 ዓ.ም ከተደረገውና አመልካች ከካዱት

---

• የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅጽ 7 ሚያዚያ 2001 ዓ.ም ገጽ 136-139

♣ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በሕግና ገቨርናንስ ኮሌጅ በሕግ ትምህርት ቤት መምህር

የመንደር ውል ይልቅ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ ትዳር የሌላቸው መሆኑን አረጋግጠው የፈፀሙት የሽያጭ ውል ለሕግና ለሞራል ለቅን ልቦናም ተቃራኒ ነው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን የቅን ልቦና መከራከሪያ ወደ ጎን በመተው የሽያጭ ውሉ ይፈርሳል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የጠ/ፍ/ቤትን ውሳኔ ሲሽር የከ/ፍ/ቤቱን ውሳኔ ግን አፅንቷል፡፡

ከላይ በተመለከተው የሰበር ሰሚ ውሳኔ ላይ ሁለት ነጥቦች ተገቢው ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እነዚህም የመጀመሪያው ጋብቻን በተመለከተ ምዝገባ ለማከናወን ሥልጣን የተሰጠው አካል ማነው? ከዚህ ጋር ተያይዞም የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ (ማግባት ወይም አለማግባትን በተመለከተ) አረጋግጦ ማስረጃ በተጠየቀ ጊዜ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት አካልስ የትኛው ነው? የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድ በጋብቻ ላይ ያለ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚያደርገውን ሽያጭ በተመለከተ ያለ አንደኛው ተጋቢ ስምምነት ባደረገ ጊዜ የቤተሰብ ሕጉ ውሉን ለተዋዋለው 3ኛ ወገን (ለገዢ) በተለይም የቅን ልቦና ተዋዋይነቱን በመጥቀስ ለሚያቀርበው መከራከሪያ የሚሰጠው ጥበቃ እስከምንድረስ ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 በሚወጣበት ወቅት ሕጉ በሥራ ላይ በዋለ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕጉ ተፈፃሚ ለሚሆንባቸው መስተዳደሮች የሚያገለግል የምዝገባ ሕግ የፌዴራሉ መንግሥት ያወጣል አስፈላጊ ተቋሞችንም ያደራጃል ሲል ደንግጓል[1]፡፡ ይኸው የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ተቋቁሞ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ ሕጉ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች አግባብ ባለው አካል የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የልደት፣ ጋብቻና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም እንደተሰጡ ሰነዶች ተቆጥረው ሕጋዊነት ይኖራቸዋል በሚል ተመልክቷል[2]፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ በሕጉ ላይ እንዲቋቋም የታለመው ተቋምና የምዝገባ ሕግ ገና በሥራ ላይ አልዋሉም፡፡ ይህም ማለት ይኸው የምዝገባ ሕግ እስካልተተገበረ ድረስ አግባብ ባላቸው ሌሎች አካላት የተሰጡ የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም እንደተሰጡ ተቆጥረው ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ አመልካች ስለተጠሪ የጋብቻ ሁኔታ ጠይቀው ማስረጃ ያገኙት ከክፍሉ ቀበሌ ነው፡፡ ይህ ከቀበሌ የተሰጠው ማስረጃ ደግሞ በክብር መዝገብ ሹም ከተሰጡ ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ የሕግ ውጤት እንዲኖረው ቀበሌ ሕጉ እውቅና ከሚሰጣቸው አግባብ ያላቸው አካላት ውስጥ የሚመደብ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

አሁን ባለው አሠራር የክብር መዝገብ ምዝገባ አገልግሎት በተለያዩ ተቋማት ሲሰጥ ይታያል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት፣ ክፍለ ከተሞች፣ ቀበሌ እና የከተማ ማዘጋጃ ቤት ተጠቃሾች ናቸው፡፡[3] በመሠረቱ ቀበሌዎች በሕጉ አግባብ መሠረት የተዋቀሩ ተቋማት መሆናቸው አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡[4] ከዚህም በተጨማሪ ቀበሌዎች ከዚህ በፊት በነበረው ተለምዶአዊ አሠራር እና በቢፒአሩም (BPR) ጭምር የተለያዩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባዎችን እያካሄዱ የሚገኙ ተቋማት መሆናቸው ይህንኑ አቋም የሚያጠናክር ነው፡፡ ሆኖም ግን ሕጉ ምዝገባን በተመለከተ እንዲቋቋም ያቀደው ተቋም ባለመቋቋሙ ምክንያት ባለው የሽግግር ወቅት ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ምዝገባውን እያከናወኑ እንዲቆዩ ቢፈቅድም እነዚህ ተቋማት ዋነኛ ሥራቸው ምዝገባን ማከናወን ካለመሆኑ አንፃርና ለዚህም የሚሆን በቂ

[1] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ 213/92 አንቀጽ 321(1)፡፡ ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁ 213/92 ተብሎ የሚጠቅስ

[2] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 321(2)

[3] ለዚህ ዋነኛ መሰረቱ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 3361 ላይ የተቀመጠው የመሸጋገሪያ ሕግ ነው፡፡

[4] በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሚገኙትን ቀበሌዎችን በተመለከተ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 15/2001 እና 21/2002 መሠረት በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ያልተዋቀሩ ከመሆኑ አኳያ በማስረጃ አሰባሰብ፣ አቀማመጥና አሰጣጥ አኳያ ሰፊ ክፍተት እንደሚኖር ለመረዳት ብዙም የሚያዳግት አይሆንም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው ጋብቻ አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ቀበሌ ተቋማዊ ችሎታ አለው ወይ? የሚለው በራሱ ሊፈተሽ የሚገባው ጉዳይ ነው:: ለዚህም ተከታዩን ሁኔታ መመልከት ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎች ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈፀምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈፀም እንደሚችል በቤተሰብ ሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡[5] ይህም የሚያሳየው አንድ ሰው ይኖርበት ከነበረው አካባቢ ውጭ ጋብቻውን ሊፈፅም የሚችልበት ዕድል እጅግ በጣም ሰፊ መሆኑን ነው፡፡ ጋብቻቸው በሀይማኖት ወይም በባህል መሠረት የተፈፀመ ከሆነ ደግሞ በተለይ ቀበሌዎች የእነዚህን ተጋቢዎች የማግባት ወይም ያለማግባት ሁኔታ በተመለከተ መረጃ ለመስጠት ያላቸውን አቅም እጅግ ውሱን ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ጋብቻው የሚፈፀመው ባህሉ ወይም ሀይማኖቱ በሚያዘው ሥርዓት መሠረት እንጂ ሕጉ ልክ እንደ ክብር መዝገብ ሹም ፊት እንደሚፈፀም ጋብቻ የሚያስቀምጠው የቦታ ክልከላ ባለመኖሩ ተጋቢዎች በመረጡት ቦታ ሊፈፅሙት በመቻላቸው ነው፡፡ ምንም እንኳ የሀይማኖትም ሆነ የባህል ጋብቻ በሕጉ መሠረት መመዝገብ ያለባቸው ቢሆንም [6] ይኸው መዝጋቢ አካል እስኪቋቋም ጊዜ ድረስ ግን ምዝገባው በቀበሌ አማካኝነት ሊከናወን ቢችልም የግድ በተጋቡበት ቀበሌ ጋብቻቸውን ያስመዝግቡ የሚል ሕግ ባለመኖሩ ከቀበሌ የሚቀርቡ ያለማግባት ማስረጃዎች ሁልጊዜም ፍፁም አስረጂ (conclusive evidence) ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ አይሆንም፡፡ ስለሆነም በቀበሌ በኩል በዚህ መልኩ የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደ አንድ አስረጂ ተደርገው ከመወሰድ ባሻገር በተለይ በጋብቻ መካከል ለሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደ ፍፁም ማስረጃ ተወስደው በሰበር ሰሚው ችሎት ደረጃ ለውሳኔ መስጫ እንደ አንኳር ነጥብ ተደርገው ሊወሰዱ የሚገባ አይመስልም፡፡

ከዚህ አንፃር የሰበር ሰሚ ችሎቱ ‹‹… አመልካቹ ቤቱን ሲገዙ ከቀበሌ ማስረጃ መጠየቃቸው የቀበሌ ጽ/ቤት የነዋሪዎችን አሰፋፈርና አኗኗር ሁኔታ በተመለከተ *ለማንኛውም ተቋም በተሻለ* መረጃዎችን ሰብስቦ የሚመዘግብ ከመሆኑ አንፃር መረጃው አግባብነት ያለው ነው›› (ሰረዝ የተጨመረ) በሚል ያሰፈረው ትችት የቀበሌ ጽ/ቤት በተግባር ያለበትን የባለሙያ እና የአደረጃጀት፣ ከምንም በላይ ደግሞ ዋነኛ ተግባሩ የወሳኝ ኩነቶች መዝጋቢ መሥሪያ ቤት ሆኖ ያልተዋቀረ ተቋም ከመሆኑ ጋር ሲደመር ትንታኔው አግባብ አይመስልም፡፡ ይልቁንም ከቀበሌ ጽ/ቤት የሚሰጡ ሰነዶች እንደ ፍፁም አስረጂ ተወስደው መብት ሊቋቋምባቸው እንደሚችሉ አድርጎ መቀበል ሕጉን ብቻ ሳይሆን ነባራዊ ሁኔታውንም ከግምት ውስጥ አለማስገባት ነው የሚሆነው፡፡ ስለሆነም ከላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው ከቀበሌ የሚሰጡ ሰነዶች የአስተማማኝነት ደረጃቸው እጅግ ውስን በመሆኑ በተለይ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ለሚነሱ የቅን ልቦና መከራከሪያዎች እንደ መነሻነት ለማገልገል ብዙም ብቃት ያላቸው አይመስልም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 68(ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥም ሆነ ለመለወጥ የሁለቱም ተጋቢዎች የጋራ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ይህንን ስምምነት በመተላለፍ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለሌላ ሦስተኛ ወገን ተላልፎ ቢገኝ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው በግልፅ በአንቀጽ 69 ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ይኸውም ስምምነቱን ያልሰጠው ወገን ግዴታው እንዲፈርስ ለፍ/ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ መነሻነት ውሉ ሊፈርስ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሁለቱን አንቀጾች ዓላማ አቶ መሐሪ ረዳኢ በመጽሐፋቸው ላይ ሲያብራሩ ሁለት ተወዳዳሪ ጥቅሞችን በሚያስታርቅ መልኩ የተቀረፁ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል የተጋቢዎች የጋራ ንብረት በተቻለ መጠን በተጋቢዎች የጋራ ውሳኔ ብቻ እጅ መቀየር እንዳለበት የማድረግ

[5] አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 22(1)
[6] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 28

ፍላጎት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሽያጭና የንግድ ልውውጥን ዋስትና የመስጠት አስፈላጊነት ጉዳይ ነው፡፡[7] በዚህም መሠረት የተጋቢዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ውሉን በፍ/ቤት የማስፈረስ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን የጋራ በሆነ ንብረት ላይ ውል የገባ ወገን ደግሞ (ገዢ) ያለው አማራጭ ሕጉ በአስቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ መብቱን ያልጠየቀ ተጋቢን የይርጋ መከራከሪያ በማንሳት መብቱን ማስጠበቅ ነው፡፡ እዚህ ላይ በጥሞና መታየት ያለበት አንቀጽ 69(2) በምንም መልኩ የቅን ልቦናን ጉዳይ በመከራከሪያነት ሊያገለግል እንደሚችል ያላመላከተ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሕግ ተርጓሚው ሕግ አውጪው ያላካተተውን ግብና ዓላማ ሕግን በመተርጎም ስበብ ወይም በደፈናው በተከራካሪዎች መካከል ፍትሀዊነትን ለማስፈን በሚል ብቻ ሊያካትት የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው ሕግ ተርጓሚው አካል በየትኛውም የሕግ አንቀጽ ላይ የሚገኙ ቃላት ከተራ የቃላት ድርደራ ባሻገር ሕግ አውጭው ያካተታቸው ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ሳያካትታቸው የቀረው ሆነ ብሎ አስቦና አቅዶ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ትርጓሜ ሊሰጥ የሚገባው፡፡

ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የቅን ልቦና ተከራካሪነት ዋጋ አለው ብሎ ሕግ አውጭው በአመነባቸው ቦታዎች ላይ ይህንኑ መብት በዝምታ ሳይሆን በግልፅና ቀጥተኛ በሆነ አገላለፅ አስፍሯቸው መገኘቱ ነው፡፡[8] ከዚህ አንፃር ሕግ አውጪው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 ላይ የቅን ልቦና መከራከሪያን ሳያነሳ በዝምታ ማለፉ ይህን ላለማካተት መፈለጉን በግልፅ የሚያስረዳ ነው፡፡

ይህንን የሕግ አውጭውን ዓላማ ከሕገ-መንግሥቱም ቢሆን ለመረዳት ብዙም አዳጋች አይሆንም፡፡[9] በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 34 ላይ ‹‹ቤተሰብ የሕብረተሰብ ተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው፡፡ ከሕብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ ጋብቻ ደግሞ ቤተሰብ ከሚመወረትባቸው አንዱና ዓይነተኛ መንገድ ነው፡፡ ይህም ማለት ጋብቻ የቤተሰብ መነሻ እንደመሆኑ ሕገ-መንግሥታዊ ጥበቃ እና እንክብካቤ የሚደረግለት ተቋም ስለመሆኑ ብዙም ማብራራት የሚፈልግ ጉዳይ አይሆንም፡፡

ለጋብቻ የሚደረግ ጥበቃ ማለት ደግሞ ተጋቢዎች በጋብቻ ጊዜ የሚኖራቸውን የግል እና የንብረት ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ የተጋቢዎች የጋራ ንብረት በዋነኛነት የትዳር ውጪ የሚሸፈንበት ከመሆኑ አንፃር ለትዳሩ መቀጠልና አለመቀጠል እንደ ማዕዘን ድንጋይ የሚያገለግል ነው ቢባል ብዙም ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የጋራ ንብረት እንደው በዘፈቀደ በሕጉ ላይ ባልተካተቱ ነጥቦች ህልውናውን እንዲያጣ ማድረግ ሕገ-መንግሥት ለቤተሰብ ጥበቃ ሲል ያስቀመጠውን ድንጋጌ እጅጉን መፈታተን ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው ሕገመንግሥቱ ለቤተሰብ እና ለጋብቻ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች ተንተርሶ የወጣው የቤተሰብ ሕግ የጋራ ንብረትን በተመለከተ የሚደረጉ ልውውጦችና ግዴታዎች የሁለቱን ተጋቢዎች ፈቃድ የሚጠይቁ አድርጎ የቀረፃቸው፡፡ ለዚህም ነው የቅን ልቦና መከራከሪያ አንግበው መብት ከሚጠይቁ 3ኛ ወገኖች (ገዢ) ይልቅ ሕገመንግሥታዊ ጥበቃ ከተሰጣቸው ቤተሰብና ጋብቻ የሚመነጩ የተጋቢዎች መብቶች የተሻለ፣ የላቁና ሚዛን የሚደፉ የሚሆኑት፡፡

የቅን ልቦና ተከራካሪዎች በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 የሚሸፈኑ ካልሆኑ ያላቸው አማራጮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚለውን እንመልከት፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 የተቀመጠው ውልን

---

[7] መሐሪ ረዳኢ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ለመገንዘብ የሚያስችሉ አንዳንድ ነጥቦች ቅጽ 1 ሁለተኛ ዕትም 2002

[8] የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1161-1666 በምሳሌነት መመልከት ይቻላል፡፡ ሆኖም በእነዚህ አንቀፆች ላይ የተመለከተው የቅን ልቦና ተከራካሪነት መብት የሚሰራው በተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ ለዚያውም መደበኛ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ላይ ብቻ እንጂ በልዩ ተንቀሳቃሽ ወይም በማናቸውም ሁኔታ በማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲሁም ግዙፍነት ለሌላቸውን ንብረቶች የሚያገለግል አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ልዩ ተንቀሳቃሽ፣ የማይንቀሳቀስ እንዲሁም ግዙፍነት የሌላቸው ንብረቶች ባለቤትነት ለመያዝ፣ ለማስተላለፍ፣ ለመሸጥም ሆነ ለመለወጥ እራሳቸውን የቻለ ልዩ ሕግ ያላቸው ከመሆኑም ባሻገር ምዝገባን የግድ ስለሚሉ ነው፡፡ በተጨማሪነትም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 345 እና 346ን ማየት ይቻላል፡፡

[9] የኢትዮጵያ ፌደራልዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 34 እና 35ን ይመለቷል፡፡

የማፍረሻ አማራጭ በአጠቃላይ በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ከተመለከቱት የውል ማፍረሻ ምክንያቶች በተጨማሪነት የሚያገለግል መሆኑ ብዙም አከራካሪ አይሆንም።[10] ስለሆነም የውሉ መፍረስ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው ለሚለው ምላሽ ለመስጠት የፍትሐብሔር ሕጉን ድንጋጌዎች በጥሞና መመልከት ያስፈልጋል።

አንድ ውል የመሰረዙ ወይም የመፍረሱ ውጤት በመጀመሪያ ተዋዋዮቹ በተቻለ መጠን ውለታ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው።[11] ይህም ማለት በጋራ ንብረት ላይ በቅን ልቦና ውለታ ያደረገ ሦስተኛ ወገን ስምምነቱን ባልሰጠው ተጋቢ አማካኝነት በቀረበ ክስ ውሉ እንዲፈርስ በፍ/ቤት ሲታዘዝ አስቀድሞ ውለታው ያመጣቸውን ወጪዎች መልሶ የማግኘት መብት ይኖረዋል ማለት ነው። ሆኖም በውለታው አማካኝነት እጁ የገባውን ንብረት መልሶ የመስጠት ግዴታ ይኖርበታል። ሌላው በተለያዩ ምክንያቶች ውለታውን ለመፈፀም የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን የተሠሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ለማዘዝ ፍ/ቤት ሥልጣን ያለው መሆኑ ነው።[12] በእርግጥ እዚህ ላይ መታየት ያለበት የቅን ልቦና መኖር ብቻ በራሱ የተሠራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል አያደርገውም። ይልቁንም ይኸው ተከራካሪ ከቅን ልቦናው ባሻገር ውለታ በተደረገበት ነገር ላይ ያደረገው ለውጥ ወይም ማሻሻል ተዋዋዮችን ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ የማያስችል መሆን ይኖርበታል።

የውሉ መፍረስ የቅን ልቦና ተከራካሪዎችን በባዶ የሚያስቀር አይሆንም። በእርግጥ ውለታ የተደረገበትን ጉዳይ በእጅ አድርጎ የመቀጠል ነገር እጅጉን የጠበበ ቢሆንም ዕድሉ ሙሉ በሙሉ የተዘጋ ግን አይደለም። በመሆኑም ፍ/ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ አሊያም ውለታውን ማፍረስ የማይቻል በሆነ ጊዜ ደግሞ ተገቢውን ኪሳራ በማስከፈል በተቻለ መጠን ተዋዋዮቹ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ ለመመለስ የሚችልበት ሁኔታ አለ።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል አንድ አንኳራዊ መከራከሪያ ሊኖር ይችላል። ይኸውም በተለይ አላግባብ ጥቅም የሚፈልጉ ተጋቢዎች በተለይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከጊዜ መጨመር ጋር የሚያሳየውን የዋጋ ለውጥ አላግባብ ለመጠቀም የሚያስቡ በሚሆንበት ጊዜ ንብረቱ በጊዜው በትዳር ጓደኛ ሲሸጥ ሲለወጥ እያወቁ ሆኖም ግን በውሉ ላይ ፊርማቸውን አለማኖራቸውን በመንተራስ ብቻ ውል የማፍረስ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ብልጣብልጥና የማይገባ ጥቅም ፈላጊ ባለትዳሮች ከላይ የተቀመጠው አተረጓጎም ያልተገባ ይሁንታ የሚሰጥ አይሆንም ወይ? የሚለው ነው። እዚህ ላይ ግን መሳት የሌለበት አንድ መሠረታዊ መርሆ አለ። ይኸውም ሕግ ግልፅ በሆነበት ጊዜ ትርጓሜ አያስፈልገውም የሚለው ነው። ሕጉ ግልጽ በሆነ ጊዜ ትርጉም አያስፈልግም የሚለው መርህ ቢኖርም የሕጉ ግልፅ ድንጋጌ አጠቃቀም ወደ ኢ-ምክንያታዊ ድምዳሜ የሚያደርስ ከሆነ ሕጉ ግልፅ ቢሆንም በእርግጥ ትርጓሜ ያስፈልገዋል። ሆኖም ግን አሁን በተያዘው ጉዳይ የሕጉ ግልፅ ድንጋጌ ተግባራዊ ቢሆን ይህ አተረጓጎም ኢ-ምክንያታዊ ውጤት ላይ ያደርሳል ሊባል የሚችልበት አጋጣሚ አልተፈጠረም። ምክንያቱም በግልፅ ተለይተው ከሚታወቁት ተወዳዳሪ ጥቅሞች መካከል ሕጉ ለቤተሰብ፣ ለትዳር እና ለጋራ ንብረት ሊሰጠው የፈለገው ጥበቃ የተሻለ እና የበለጠ ነው።

ግልፅ የሆነ ሕግን ለአንደኛው ወገን አድሎአዊ ነው ወይም አንደኛውን ወገን ጠቃሚ ነው በሚል ብቻ በትርጉም ስበብ ማሻሻል የሕግ ተርጓሚው መብት፣ ሥልጣንም ሆነ ኃላፊነት አይደለም። በተለይ አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው ሕግ አውጭው አንቀጽ 69ን በሚቀርፅበት ጊዜ ሆነ ብሎ ለተጋቢዎች መብት ሰፋ ያለ ጥበቃ የሰጠ

---

[10] መሐሪ ረዳኢ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ለመንገዘብ የሚያስችሉ አንዳንድ ነጥቦች ቅጽ አንድ ሁለተኛ ዕትም 2002 ገጽ 80 በተጨማሪም የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1676 እና 1808-1818 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመለከቷል።
[11] የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1815 (1)
[12] የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 1817 (1)

መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ በእርግጥ ሕግ አውጪው ይህንን ሰፊ መብት ለተጋቢዎች ሲሰጥ በተለይ የቅን ልቦና ተዋዋዮች ላይ የሚደርስውን የጎንዮሽ ጉዳት በጊዜው አልተመለከተም ነበር፡፡ ይህንን ኢፍትሀዊ ሁኔታ እንዲሁ ሕጉ ግልፅ ነው በሚል ምክንያት ብቻ ማስቀጠል አግባብነት የለውም የሚል መከራከሪያ ካለ ግን መፍትሔው ያለው ሕግ ተርጓሚው አካል ጋር ሳይሆን ሕግ አውጭው ዘንድ ነው፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ መታየት አለበት ተብሎ የሚታመንበት ከሆነ ተገቢው ውይይት፣ ምክክር እና ጥናት ተደርጎበት ሌሎች መሻሻል ካለባቸው እንቀፆች ጋር የቅን ልቦና ተከራካሪነት የአንቀጽ 69 ልዩ ሁኔታ ተደርጎ ሊሻሻል ይችላል፡፡ ይህ እስካልተደረገ ድረስ ግን አንቀጽ 69 ከተቀረፀበት ዓላማ አንፃር ሊተረጎም ይገባል፡፡

## ማጠቃለያ

በሁሉም ፍ/ቤቶች የሚቀርቡ ቤተሰብ ነክ ጉዳዮች ከፍሬ ነገር ከማስረጃና ከሕግ ክርክር አልፎ ማህበራዊ፣ባህላዊ፣ሀይማኖታዊ፣ስሜታዊ ወዘተ...ገፅታዎች የሚንፀባረቁባቸው በመሆኑ የክርክሩ አመራርና የውሳኔ አሰጣጥ ከፍተኛ ዕውቀት፣ ክህሎትና ጥንቃቄን የሚጠይቁ ናቸው፡፡[13] በተለይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ የሚያሰፍራቸው የሕግ ትርጉሞች በሁሉም የሀገሪቱ ፍ/ቤቶች አስገዳጅነት ያላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገባቸው ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ሰበር ሰሚ ችሎት ለሚሰጣቸው ውሳኔዎች ከሌሎች ፍ/ቤቶች ይልቅ የበለጠ ኃላፊነት የሚኖርበት፡፡ በተያዘው ጉዳይ ላይ የሰበር ችሎቱ ለሰጠው የሕግ ትርጓሜ በዋነኛነት እንደምክንያት ተደርጎ ሊቆጠር የሚገባው የቤተሰብ ሕጉ ሲወጣ ይቋቋማል የተባለው መዝጋቢ አካል ተቋቁሞ ሥራ አለመጀመሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ይኸው መዝጋቢ አካል ተቋቁሞ ቢሆን ኖሮ የምዝገባ አድማሱ አንድ ወጥና ሀገር አቀፋዊ በመሆኑ የትኛውም ወገን ውለታ ከማድረጉ በፊት ውለታ የሚያደርገውን ሰው የትዳር ሁኔታ በተመለከተ መረጃ ከዚሁ አካል በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ በቅን ልቦና ትዳር ያለው ስላልመሰለኝ ነው ውለታ ያደረኩት የሚል መከራከሪያ የሚነሳበት አጋጣሚ ፈፅሞ ይጠፋል ባይባልም በእጅጉ የጠበበ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ይኸው መዝጋቢ አካል ባለመቋቋሙ ምክንያት በዋነኛነት ተጎጂ የሚሆኑት ወገኖች ከባለትዳሮች ጋር በጋራ ንብረት ላይ ውለታ የሚያደርጉ ወገኖች እንደመሆናቸው የሰበር ሰሚ ችሎቱም የእነዚህን ወገኖች መብት ለማስጠበቅ ሲል ሕጉን እንደማሻሻል የሚቆጠር ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡

የቅን ልቦና ተከራካሪነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት በሚል የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሕግ ከመተርጎም ይልቅ ሕግ ወደ ማውጣቱ የሚያዘነብል ይመስላል፡፡ ምክንያቱም የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68 እና 69ን በጥሞና በመመልከት ሕግ አውጭው በግልጽ ነጥቡን አለማካተቱ ጉዳዩን በመከራከሪያነት እንዲቀርብ አለመፈለጉን የሚያሳይ ሆኖ ሳለ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ሕጉ ግልጽ በሆነ ጊዜ ትርጉም አያስፈልግም የሚለውን መርህ በሚጥስ መልኩ የቅን ልቦና ጉዳይን ማካተቱ ሕግ ከመተርጎም ይልቅ ሊባል የሚችለው ሕግ ማውጣት ነው፡፡ ይህም ፍርድ ቤት በሕግ ከተሰጠው ሥልጣን አኳያ አግባብነት የሚኖረው አይሆንም፡፡ ■

[13] ፌሊጶስ አይናለም ሳይፋቱ (ዲፋክቶ) ፍቺ Mizan Law Review, Vol.2, No. 1 2008፣ ገፅ. 110